# ፍትህና ሀገር አቀፍ ውይይት
## መጋቢት 12/2014 ዓ.ም

## በዳዊት ወልደጊዮርጊስ

አገሮችና መንግስታት ቀውስ ላይ የሚወድቁት ፍትህ ሲጠፋ ነው:: ፍትህ ማለት ነፃነት ነው:: ፍትህ የህዝብ መጨቆኛ መሳሪያ አይደለም:: ፍትህ ማለት ወንጀለኞችን መቅጫ መሳሪያ ነው:: ፍትህ ለሁሉም እኩል ናት:: ፍትህ ማለት በነፃነት መናገርና መደመጥ ነው:: ፍትህ ማለት በደልን ማጥፋትና የህዝብን አንድነትና ሰላም መጠበቅ ማለት ነው:: ፍትህ ለመሪዎች መሳሪያ መሆን ስትጀምር የሀገርና የህዝብ አንድነት ምሶሶ የሆነው የህዝብ የበላይነት ይናዳል:: ፍትህ መድህን መሆንዋ ቀርቶ የጨቆኞች መሳሪያ ትሆናለች::
ይህንን ሚዛን የሚያስጠብቀው ህዝባዊ ህገ መንግስትና ህዝባዊ ምርጫ ነው:: ህግ አውጪውም: ፍርድ ሰጪውም: ህግ አስፈፃሚውም በግልፅም ሆነ በተሸፋፈነ መልክ በአንድ ወይም በጥቂቶች እጅ ስትወድቅ የአገር መፈራረስንና የህዝብ እልቂትን ያስከትላል:: ሶስቱ ክፍሎች ተለያይተው በፍፁም ነፃነት ህዝብ በመረጠው ህገ መንግስት ሊሰሩ እንዲችሉ ምን አይነት ህዝባዊ ጉባኤ ሊደረግ እንደሚገባው ይህች ፅሁፍ በመጀመሪያ በእንግሊዝኛ የተፃፈውን ለአንባቢዎች አቀርባለሁ::

## ቀጪ ፍትህ (Retributive Justice)

ያለ ሰላም እና ፍትህ መረጋጋት ሊኖር አይችልም። የማንኛውም ሀገር አቀፍ ውይይት ዓላማ ወደ ሰላም እና መረጋጋት የሚደረግ ሽግግር መሆን አለበት፣ ይህን ለማሳካት ብቸኛው መሣሪያ ፍትህ ብቻ ነው። ፍትህ መኖር አለበት፣ የጥላቻ አይዲዮሎጂ የሚያስተዋውቁ ሰዎች ከቅጣት ማምለጥ አይችሉም፣ በሀገሪቱ ለደረሰው በመቶ ሺዎች የሚቆጠር እልቂት እና ዘረፋ ኃላፊነት አለባቸው። የእነዚህ ወንጀሎች ፈፃሚዎች ወደ ወንጀል ፍርድ መቅረብ አለባቸው፣ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ መቀጣት አለባቸው። እነዚህ ችሎቶችና የጥፋተኝነት (የቅጣት) ውሣኔዎች ብዙውን ጊዜ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ለመፈፀም የተባበሩትን በማስቀጣት ላይ የሚያተኩር ሲሆን የሽግግርና የመልሶ ማቋቋም ፍትህ ግን በተጐጂዎች ፍላጐቶች፣ በግጭት መሠረታዊ መንስኤዎች እና ጥፋተኞችን ከሕብረተሰቡ ጋር በማቀላቀል መልሶ ለማቋቋም በሚቻልበት እድል ላይ ያተኩራል። የዚህ ዓይነቱ ፍትህ ፅንሰ ሐሳብ ወንጀል በድጋሚ እንዳይፈፀም ለመከላከል፣ ጥፋተኞችን ለመቅጣትና መልሶ ለማቋቋም እንዲሁም ሰዎች በሰላም አብሮ መኖርን እንዲማሩ ማድረግ ነው።
የመጨረሻው ዓላማው የሚከተሉትን ይጨምራል፦ የሕጋዊነትን እሴት እና የሕግ የበላይነትን ማስፋፋት እና ጉዳዩን መዝጋት። ተጐጂዎችና ወንጀለኞች ከተስማሙ እውነቱን ሙሉ በሙሉ ለማግኘትና እርቅ ለመጀመር ውይይት ማነሳሳት ይችላሉ። ለራሷ ሰላም ያለባት ሀገር ለመፍጠርና በአንድነትና በሕብረት ወደፊት ለመንቀሳቀስ ፍትህ ለማንኛውም ሌላ አማራጭ

መቅደም አለበት። የሕግ የበላይነት በሌለበት ሀገር አይኖርም። ማንኛውም ዜጋ ለማፍቀርና ለመታረቅ ሊገደድ አይችልም። የግል ምርጫዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን የሕግ የበላይነት ሰዎች በፍቅር፣ በይቅርታ እና በእርቅ በማያምኑ ሰዎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥበቃ ያደርግላቸዋል።

« ይቅር ባይነት ማለት ልባዊና ስለሆነው ነገር መግባባት ላይ የሚደረስበት እንዲሁም የደህንነት ስሜት የሚዳብርበት እና ጥላቻ የሚወገድበት (ከሁሉም በላይ እንዴት ይቅር ማለት እንደሚቻል የሚታወቅበት) የውስጥ ሂደት ነው። አጥፊው ወገን የግድ የዚህ ሂደት አካል መሆን የለበትም። »

በሌላ በኩል እርቅ፣ ስለሆነው ነገር ከአጥፊው ጋር ውይይት የሚደረግበት፣ ታሪኮች፣ የሚጋሩበት፣ ጉዳት የሚገለፅበት፣ ቁጭት የሚደመጥበትና መተማመን እንደገና መፈጠር የሚጀመርበት በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ሂደት ነው። ይህ የበለጠ ውስብስብ ሂደት ሲሆን፣ ይቅር ባይነትን የሚጨምር ሆኖ ከዚያም በላይ የሚሄድ ነው። 'ይቅር ባይነት ብቸኛ ሂደት ሲሆን፣ እርቅ ግን ጥምር ጥረት ነው'። ሰይድ ስሜድስ በአንድ ወቅት እንደተናገረው « ይቅርታ ለማድረግ አንድ ሰው ይበቃል፣ እንደገና መዋሀድ ግን ሁለት ሰዎችን ይጠይቃል »። ለሞተ ወይም እስከወዲያኛው ለማታገኘው ሰው ይቅርታ ማድረግ ይቻላል። ወይም ይቅርታ የማድረግ ሐሳብ ለሌለው ሰውም እንዲሁ። ስለዚህ ይቅርታ የግድ አስፈላጊ አይደለም፣ ነገር ግን ካለ ይረዳል። »

ሰዎች የሚገዙት በሰዎች ፍላጐት ሳይሆን በሕግ የበላይነት ነው። የቅቡል የሕግ የበላይነት ጽንሰ ሐሳብ እራሱን በሕግ በሚገዛ ማሕበረሰብ ሐሳብ ላይ የተመሰረተ ነው። በግጭት ውስጥ ባለፉና ዋና የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት በሚጥሩ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ቅቡል የሕግ የበላይነት ሙሉ በሙሉ አልዳበረም። መንግሥት የችግሩ አካል በመሆኑ አስፈላጊ ለውጥ ለማምጣት ቅቡልነት የለውም። መንግሥታት የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የመቅጣት ኃላፊነት አለባቸው። ይህን ለማድረግ ካልቻሉ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ የብሔራዊ ውይይት የማካሄድና የመከታተል ተግባር እንዲሁም የሁለንተናዊ ሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ተግባር በዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት ላላቸው ገለልተኛ አካላት መተላለፍ አለበት። ከእነዚህ አንዱ አይሲሲ ነው።

« ዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት (አይሲሲ) ተቋቁሟል። ይህ በሕገ ደንቡ የተገለጹ ከባድ ዓለም አቀፍ ወንጀሎች በፈፀሙ ሰዎች ላይ ሥልጣን ያለው ቋሚ ተቋም ሲሆን፣ የብሔራዊ የወንጀል ሥልጣን ተጨማሪ ሆኖ ይሠራል። የፍርድ ቤቱ ሥልጣን እና ተግባር በዚህ ሕገ-ደንብ ድንጋጌዎች ይገዛል ።» (2002)

በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፉ ሀገሮች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡- ሩዋንዳ፣ ዲአርሲ፣ የቀድሞዋ ዩጐዝላቪያ፣ ሱዳን፣ ኬኒያ፣ ላይቤሪያ እና ማይናማር።

በግጭት የተሞላ ታሪክ ያለው የተከፋፈለ ሕብረተሰብ ይህንኑ ታሪኩን ለማውሳት እንዴት ወደፊት መራመድ እንደሚቻል የሚያሳይ አንድ ወርቃማ ደረጃ ከ25 ዓመታት በፊት በደቡብ አፍሪካ የተካሄደው የእውነት ፍለጋና የእርቅ ኮሚሽን፣ ከዚያም ወዲህ የሩዋንዳ እና ላይቤሪያ ተሞክሮ ሲሆን፣ ይህ ከመላው ዓለም የሚደረጉ ሌሎች ተመሳሳይ ጥረቶችን የሚያነቃቃ ነው። እነዚህ ሀገሮች በጊዜ ሂደት በውስብስብ ጉዳዮች ውስጥ ካለፈ ታሪካቸው መማር ችለዋል።

ሆኖም በየሀገሮቻቸው በግለሰብና በስርዓት ደረጃ በተፈፀሙ ጥፋቶች ላይ ለመነጋገር የሚቻልበትን መንገድ ከፍተዋል።
የደቡብ አፍሪካ የእውነት ፍለጋ እና የእርቅ ኮሚሽን (ቲአርሲ) አዝጋሚ ዲሞክራታይዜሽን ወይም ድርድር የተደረገበት የግጭት አፈታት እየተባለ ሊጠቀስ የሚችለው የዚህ ሂደት ውጤት ነው። የቀድሞ መሪዎች ሰላማዊ ሽግግርን ለማረጋገጥ የራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል። በዚሁ ሁኔታ የወደፊቱን ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ቀጪ ፍትህ ቀሪ ሊደረግ ይችላል። ሆኖም ፍትህ እና ቅጣት ባለመኖሩ ሙከራው የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልቻለም።
በእኔ አስተያየትና በዚያ ሀገር ለመኖር እድል ባገኙ ሌሎች በርካታ ሰዎች አስተያየት፣ እንዲሁም ጉልህ ብዛት ባለው የሕበረተሰብ ክፍል እምነት፣ የደቡብ አፍሪካ የእውነት ፍለጋ እና የእርቅ ኮሚሽን ጥረት በሕዝቡ መካከል ሰላምና እርቅ ለማምጣት በቂ አልነበረም። ደቡብ አፍሪካ አሁንም በመላው ዓለም እኩልነት ከሌለባቸው ሀገሮች ዋነኛዋና ቁጣ እና ቅሬታ አደገኛ ደረጃ ላይ የደረሰባት ወንጀል በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋባት ሀገር ናት። ሆኖም ሕዝቡ ሐሳብን የመግለጽ ሙሉ መብት ያለው ሲሆን፣ በማንኛውም መልክ ሐሳቡንና ቅሬታውን በጽሑፍ እና በተለያየ መንገድ የመግለጽ መብት እንዳለው አረጋግጧል። መንግሥትም ያዳምጣል፣ ነገር ግን ስር በሰደደ የእኩልነት አለመኖር ፖሊሲና አመለካከት ምክንያት የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት አልቻለም። ቲአርሲ ፍኖተ ካርታ መሥራት የሚጠበቅበትን የመሠረታዊ ለውጥ ጥሪ በተሳካ ሁኔታ መቋቋም ችሏል። ፍኖተ ካርታ በሌለበት ደቡብ አፍሪካ ስር ነቀል ለውጥ ካልተካሄደ፣ በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ የሚችልባት ተሰባሪ ዲሞክራሲ ለመሆን በቅታለች። ቲአርሲ ፍትህንም ሆነ እርቅን ማምጣት አልቻለም። በእርቅ እና ፍትህ መካከል ተገቢ ሚዛን መጠበቅ አልቻለም።

ዊኒ ማንዴላ በአንድ ወቅት እንደተናገሩት፡-
«እውነት ፍለጋና እርቅ የሚባለውን ተራ ውሸት ተመልከቱ። በዚህ ፈፅሞ መስማማት አልነበረበትም።» ንዴታቸው ያነጣጠረው በቀድሞ ባለቤታቸው በማንዴላ ላይ ነበር። «እውነቱ ምን ይሠራል? ማንኛውም ሰው የሚወዳቸው ቤተሰቦቹ እንዴት እንደተገደሉ ወይም እንደተቀበሩ ለማወቅ ምን ያህል ይረዳዋል? እኚያ ጳጳስ ቱቱ ናቸው ሁሉንም ነገር ወደ ሃይማኖታዊ ሰርከስ የቀየሩት።»
ነገር ግን ከላይ እንደገለጽኩት ሀገሪቱ ጥሩ ጅምር ነበራት። ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ ሁሉም ሀገሮች ትምህርት እንደተማሩ አምናለሁ። እስካሁን እንዳደረጉት፣ ይህንኑ «በተቀሰመ ትምህርት» አማካኝነት ማረም እንደሚያስፈልጋቸው አውቃለሁ። ሰላምና መረጋጋት ሊገኝ የሚችለው በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ክፋት ተለይቶ ሲታረም ብቻ ነው። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በግፍ ከተጨፈጨፉበት አምባገነናዊ ስርዓት ለመላቀቅ የሚሞክር አገር ያለ ፍትህ፣ ቅጣትና ከዚያም እርቅ ውጪ ሊሆንለት አይችልም።
በኢትዮጵያ የጥላቻ ርዕዮተ ዓለም ለሚያራምዱና ለዘረፉ፣ ብዙዎችን ለገደሉና ላሰቃዩ እንደ

ኮምቦዲያው ፖል ፖት፣ እንደ ናዚ እና በሩዋንዳ፣ በላይቤሪያ፣ በሴራሊዮን እና በሌሎች በርካታ ሀገሮች እንደ ናዚ የዘር ማጥፋት ወንጀል ለፈፀሙ ወንጀለኞች ከፍትህ ውጭ ሌላ አማራጭ መኖር የለበትም። ፍትህ ከእርቅና ይቅርታ መቅደም አለበት። ይህም ለቅጣት ብቻ ሳይሆን ሰዎች ያለፈውን ታሪክ ወደ ጐን ትተው በትክክል ወደፊት ለመራመድ የሚያስችላቸው በመሆኑ ነው።

## ጠጋኝ ፍትህ (Restorative Justice)

ጠጋኝ ፍትህ የሚሠራው ብዙውን ጊዜ ለአነስተኛ ጥፋት እንጂ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ለሚፈጸም ወንጀል ወይም ሐሳብን የመግለጽ ነፃነታቸውን በሚጠቀሙ ማሕበረሰቦች ወይም ቡድኖች በጨካኝ መንግሥት ወይም ቡድኖች ሆን ተብሎ ሰዎችን በአካል ለመጉዳትና ተንበርካኪ ለማድረግ ወይም በተወሰነ ሕዝብ ወይም ዘር ላይ ለሚፈፀም የወንጀል ዓይነት አይደለም። የጠጋኝ ፍትህ ስርዓት ተጐጂዎችና አጥፊዎች አንድ ወንጀል ያስከተለውን ጉዳት ለመቅረፍ በሚደረግ ውይይት፣ ተጐጂዎች ተሞክሮአቸውን፣ ፍላጐታቸውንና መሻታቸውን በሚገልጹባቸው መድረኮች ተጐጂዎችንና አጥፊዎችን ይጠቀማል። ይህ አቀራረብ የተጐጂ - አጥፊ እርቅን በመጠቀም ወይም ተጐጂዎችን፣ አጥፊዎችን፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ ጓደኞቻቸውንና ሌሎች የማሕበረሰብ አባላትን የገፅ ለገፅ ኮንፈረንስ በማመቻቸት ሊገለፅ ይችላል።

ጠጋኝ ፍትህ ከቅድመ እስር እስከ ድህረ ቅጣት በወንጀል ፍትህ ሂደት ሊገለፅ ይችላል። ይህ ማረሚያ ቤቶችንና ማሕበረሰቦችን በመሳሰሉ የተለያዩ ስፍራዎች ሊከናወን ይችላል።

ዳኞች የጠጋኝ ፍትህ መርሆዎችን በመከተል የአንዳንድ አጥፊዎችን ቅጣት ማቅለል ይችላሉ። አካሉን ላጣ ሰው ይህን መመለስ ወይም ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ለተፈጸመባት ሴት ወይም በጭካኔ ለቀናት በብልቱ ላይ የውሃ ጠርሙስ በማንጠልጠል አረመኔአዊ ስቃይ ለደረሰበት ወንድ ማካካሻ ማምጣት አይቻልም። እነዚህን ሁለት የተለያዩ ገፅታዎች በአንድ ላይ በማምጣት ተበዳይ ለአጥፊ ይቅርታ የሚያደርግበትን ሁኔታ ለመፍጠር መሞከር አይታሰብም። ፍትህ በሌለበት እነዚህን ሁለት ማሕበረሰቦች አንድ ላይ ለማምጣት መሞከር በራሱ ወንጀል ነው። ፍትህ በሌለበት ይህን ጠባሳ፣ ሕመም ወይም ጥላቻ ማስወገድ አይቻልም። ፍትህ በሌለበት ለሰዎች ይቅርታ እና እርቅ ለመስበክ የሚደረግ ሙከራ ተቀባይነት የለውም፤ ሰዎች የቋጠሩት ጥላቻ አንድ ቀን ፈንድቶ የራሳቸውን ፍትህ ለማስፈፀም ማምራታቸው አይቀርም።

ከቀጪ ፍትህ በተቃራኒ፣ ጠጋኝ ፍትህ ሰዎች ከሕግ ጥሰት ይልቅ ተጐጂ በሚሆኑበት ደረጃ ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከት ወንጀል አድርጐ ያያል። የጠጋኝ ፍትህ ዓላማው ጥፋትን ለመወሰን ወይም ወንጀል ፈፃሚዎችን ለመቅጣት ሳይሆን፣ የሚመለከታቸውን የሁሉንም ፍላጐት የማሟላትና ፈውስ የማምጣት ግዴታዎችን መለየት ነው። በተጨማሪም በአብዛኛው የአሸናፊ-ተሸናፊ ውጤት ከሚያስከትለው በአጥፊዎችና በሀገር ሕግ መካከል የሚደረግ ክርክር የፍትህ ሂደት ይልቅ፣ ጠጋኝ ፍትህ ሰፊውን ማሕበረሰብ ጨምሮ በግጭት ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ግዴታዎችንና መፍትሄዎችን በመለየት ሂደት የሚያሳትፍ በመሆኑ ሁሉም በአሸናፊነት ከሚወጣበት ሂደት ይልቅ ውይይትንና የጋራ መግባባትን ያስፋፋል።

አጥፊዎችን በገንዘብ መቀጮ፣ በቅጣት ወይም በእስር ከመቅጣት ይልቅ ጠጋኝ ፍትህ፣ አጥፊዎችን ከሕብረተሰቡ ለማቀላቀል ይጥራል፡፡ ቁስልን ለመፈወስ ሰዎች ታሪካቸውን መናገርና የሌሎችን ታሪክ መስማት እንዳለባቸው እውቅና ይሰጣል፡፡ «የሽምግልናና የውይይት» መሣሪያዎችን በመጠቀም አጥፊዎች በይፋ ፀፀታቸውን የሚገልፁበትንና ምህረት የሚያገኙበትን እድል ይፈጥራል፣ የግጭትን መሠረታዊ መንስኤዎች ለመቅረፍ እንዲሁም ወደፊት ተመሳሳይ ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ ለማድረግ ይረዳል፡፡

ጠጋኝ ፍትህ የወንጀል ፍትህን ተክቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ስህተት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ያለፍትህ ይቅርታ ብሎ ነገር ሊኖር አይችልም፣ መኖርም የለበትም፡፡ ፍትህ አጥፊውን ወይም ሰላማዊውን ሰው የሚለየው የወንጀለኞችን ቃል መነሻ በማድረግ ሳይሆን በሕግ ሂደት ነው፡፡ ፍትህ ከተበየነ እንደ ሀገር እና እንደ ማሕበረሰብ እንዲሁም እንደግለሰብ እንዴት ወደፊት መራመድ እንደሚቻል የሚወሰነው በአሽጋጋሪ ፍትህ አማካኝነት ነው፡፡

## አሽጋጋሪ ፍትህ (Transitional Justice)

መሽጋጋሪ ፍትህ የዳኝነት እና የዳኝነት ያልሆኑ ሁለቱንም ስርዓቶች የያዘ ሲሆን፣ ይህም የዓቃቤ ሕግ፣ የፍትህ፣ የቅጣት፣ የእውነት አፈላላጊ፣ ተቋማዊ ማሻሻያ ወይም የተመሳሳይ ጥረቶችን ጥምር ይጨምራል፡፡ ጥምር በሚመረጥበት ጊዜ ዓለም አቀፍ የሕግ ደረጃዎችንና ግዴታዎችን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

«አሽጋጋሪ ፍትህ የስርዓታዊ ወይም የሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ምላሽ ነው፡፡ ለተጐጂዎች እውቅና ለመስጠትና ሰላም፣ እርቅ እና ዲሞክራሲን ለመስፋፋት ይጥራል፡፡ አሽጋጋሪ ፍትህ ልዩ የፍትህ ዓይነት ሳይሆን፣ በአስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ውስጥ ያለፉ ማሕበረሰቦች የሚከተሉት ፍትህ ነው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች እነዚህ ሽግግሮች ወዲያውኑ የሚደረጉ ሲሆኑ በሌሎች ግን በርካታ አስርታት ዓመታትን ሊወስዱ ይችላሉ፡፡»

የሚከተለው ፓራግራፍ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) ዋና ጸሐፊ የአሽጋጋሪ ፍትህ መምሪያ የተወሰደ ነው፡፡

አሽጋጋሪ የፍትህ ሂደቶችና ስርዓቶች የሚሠሩት በፖለቲካዊ ክፍተት ሳይሆን፣ ብዙውን ጊዜ በድህረ ግጭትና በሽግግር ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ ከባቢዎች ነው፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጀት የፖለቲካ አውዱን እና አሽጋጋሪ የፍትህ ስርዓት የሚያስከትላቸውን እንድምታዎች ሙሉ በሙሉ መረዳት አለበት፡፡ በቻርተሩ መሠረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በማንኛውም ጊዜ ተጠያቂነትን፣ ፍትህንና እርቅን ይደግፋል፡፡

ሰላም እና ፍትህ እርስ በእርስ ተደጋጋፊ ነገሮች ሆነው መወሰድ ይኖርባቸዋል፡፡ እርስ በእርስ ተቃራኒ አድርጐ መመልከት ስህተት ነው፡፡ እዚህ ላይ ጥያቄው ለተመድ ተጠያቂነትና ፍትህን የማስፋፋት ወይም ያለማስፋፋት ጉዳይ ሳይሆን መቼ እና እንዴት የሚለው ነው፡፡ እነዚህ እርምጃዎች የሚወሰዱበት ጊዜ መጀመሪያ በዓለም አቀፍ የሕግ ግዴታዎች አውድ እና ሀገር አቀፍ አውዶችን እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በተለይም

የተጐጂዎችን አስተያየት መነሻ ያደረገ የጊዜ ማዕቀፍ መቀመጥ አለበት። የአሽጋጋሪ ፍትህ እርምጃዎችን ውጤታማነት የሚፈቅዱ ወይም የሚገድቡ ሀገር አቀፍ ሁኔታዎች ባሉበት፣ ተመድ ለትክክለኛ ስርዓትና አሰራር መሠረት የሚጥሉ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል፣ ያበረታታል።

እነዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የአሽጋጋሪ ፍትህ እርምጃዎችን በሚመለከት ፍላጐትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚደረግ እንቅስቃሴን ያስፋፋል። ተመድ በዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በጦር ወንጀል፣ በሰብአዊ ፍጡር ላይ የሚፈፀም ወንጀል እንዲሁም በሰብአዊ መብት ጥሰት ላይ ተጠያቂነትን የማያካትት ማንኛውንም የሰላም ስምምነት ድንጋጌ ሊደግፍ አይችልም። በድህረ ግጭት እና በሽግግር ጊዜ ለተጠያቂነትና ለአሽጋጋሪ የፍትህ እርምጃ ጥበቃ እድል የሚሰጡ የሰላም ስምምነቶችን መደገፍ መቻል አለበት።

ብሔራዊ ውይይት ለኢትዮጵያ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ከማያቋርጥ አለመረጋጋት፣ ከሕይወት መጥፋት፣ ከኢኮኖሚ አደጋ እና በሚመሩት ሕዝብ፣ ሀገር እና ሀብት ላይ ያላቸውን የቁጥጥር ሥልጣን ሊያሳጣ ለሚችል ለማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ ስርዓት ሜዳቸውን አሳልፈው ለመስጠት ወደማይፈልጉ የጦር አበጋዞች መፈጠር ሊያመራ ከሚችለው አረንቋ መውጣት የሚያስችል በመሆኑ ነው። የሚያስከትለው ተቀጣጣይ ውጤት እና የውጭ ኃይሎች ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ጣልቃ ገብነት ለኢትዮጵያ፣ ለቀጠናውና ብሎም ለአህጉሩ ትልቅ ቅዥት ነው።

የብሔራዊ ውይይት ኮሚቴ አባላት የእኔ ምክር ወይም ሌክቸር የማያስፈልጋቸው፣ እውቀት ያላቸው ሰዎች መሆናቸው ይታመናል። ሆኖም ተግባራቸው ምን ያህል ከባድ እና አስቸኳይ መሆኑን ለማሳሰብና በተሰጣቸው ሥልጣን ከፍተኛ አርበኝነትና ቁርጠኝነት ቢኖራቸው እንኳን በኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት እንደማይችሉ በአፅንኦት ሊሰመርበት ይገባል። በኢትዮጵያ ሰላም እና መረጋጋትን ለማምጣት ብቸኛው መንገድ ከላይ እንደተገለፀው አሽጋጋሪ ፍትህ ነው። ታሪክ መሥራት ከፈለጉና በኢትዮጵያ አንድነት ስር ሰላም እና መረጋጋት ለማምጣት ታሪካዊ አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የተመረጡበትን ማንዴት መሰረዝ አለባቸው። ይህን ምርጫ በመቀበላቸው ያሳዩትን የአርበኝነት ስሜት ማሳነስ ተገቢ ባይሆንም ኢትዮጵያ በዘላቂ ሰላም ጐዳና እንድትጓዝ ለማየት በሚፈልጉ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ዜጐች ስም ይህን አሠራር በድጋሚ በማጤን እንዲያስተካክሉና መደረግ ያለበትን ማንኛውንም ማሻሻያ እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ።

የብሔራዊ ውይይት አባላት ገለልተኛ ግለሰቦች እንጂ በመንግሥት የተመረጡ ሳይሆኑ፣ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል በሚወክል ብሔራዊ ምክር ቤት ሥልጣን የተሰጣቸው መሆን አለባቸው። ብሔራዊ ምክር ቤቱ ገለልተኛ ሆኖ የተመረጡ ኮሚሽነሮች ተግባር ሦስት ዋና ዋና ተግባራት ያሉትን የብሔራዊ ምክር ቤት እንቅስቃሴዎችን ማስተባበር ይሆናል።

> የመጀመሪያው ክፍል የወቅቱን ሕገመንግሥት ከልሶ የማሻሻያ ሐሳብ የማቅረብ ሥልጣን ያለው የሕገመንግሥት ኮሚቴ ነው። ይህ ፕሮፖዛል በብሔራዊ ጉባኤው አባላት ሰፊ ውይይት ተደርጐበት ለሕዝበ ውሣኔ የሚቀርብ ይሆናል።

ሁለተኛው ክፍል የእውነት አፈላላጊ (Truth)፣ የፍትህ (Justice)፣ የካሳና (Reparation) የእርቅ ኮሚቴ (Reconciliation) መቋቋም ሲሆን፣ ይህ ኮሚቴ ወደ እርቅ በሚያመሩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ በሰላም አብሮ መኖር የሚቻልበትን መንገድ ይጠርጋል።

ሦስተኛው ክፍል ነፃ የምርጫ ቦርድ ማቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን መወሰን ነው።

የወቅቱ የኮሚሺኑ አባላት ይህን አቀራረብ ለመንግሥት በአሳማኝ ሁኔታ ከጠቆሙ፣ ኢትዮጵያን ከማያቋርጥ ቀውስ ሊያድን የሚችል ደፋር የአርበኝነት ሥራ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል። ትርጉም ያለው በሰላም አብሮ መኖር ረጅምና አስቸጋሪ ሂደት ሊጠይቅ የሚችል ቢሆንም፣ የዚህ አቀራረብ ጅማሮና ይህንኑ ለመተግበር ያለው ቁርጠኝነት ለሕዝቡ ከፍተኛ በራስ መተማመን ይፈጥራል። የነዚህ ፕሮፖዛሎች ዝርዝር ብዙ ነው። አባላት ባላቸው ሐብት ይህን መሥራት አለባቸው።

ዋናው እርምጃ ለመንግሥት ሳይሆን ለሕዝቡ ብቻ ኃላፊነት ያለበት ነፃ ብሔራዊ ኮንፈረንስ ማቋቋም ነው። ሕዝባችንን ወደዘላቂ ልማት ሊያመራ የሚችልና እኛ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን አጀንዳ ይዘው የሚመጡ፣ ሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት በሌለበት ችግሮቻችንን መፍታት እንደምንችል ለዓለም የሚያሳይ መሠረት ይሆናል። (አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ይህ ኮሚሽን ገለልተኛ ሆኖ ሊሰራ አይችልም። በጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕዛዝ የተሰየመ ስለሆነ የሚጠበቅበት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፈቃድ መፈጸም ነው። ከላይ የተዘረዘረውን የአሻጋሪ ፍትህ (Transitional justice) ለማስገኘት በህዝብ የተመረጡ አባላት ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ግቦች ሊያስገኙ የሚችሉ መሆን አለባቸው። አባላቱ ራሳቸው ሕዝባችንን አንድ ለማድረግ ያለው ብቸኛ አማራጭ ይህ አጠቃላይ አቀራረብ መሆኑን ራሳቸው ከተረዱ መንግሥትንም ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ፣ በኢትዮጵያ ሕግ እና በኒውዮርክ በኮሉምቢያ ዩኒቨርስቲ ዓለም አቀፍ ሕግ አጥንተዋል፤ በቦስተን ዩኒቨርስቲ የአፍሪካ ጥናት ማዕከል ጐብኝ ምሁር ናቸው።

HYPERLINK "https://www.psychologytoday.com/us/basics/empathy"https://www.psychologytoday.com/us/basics/empathy

HYPERLINK "https://www.goodreads.com/author/quotes/56576.Lewis_B_Smedes"https://www.goodreads.com/author/quotes/56576.Lewis_B_Smedes

HYPERLINK "https://www.pressreader.com/south-africa/the-star-south-africa-lateedition/20100310/281505042387578"https://www.pressreader.com/south-africa/the-star-south-africa-lateedition/20100310/281505042387578

HYPERLINK "https://www.un.org/ruleoflaw/files/TJ_Guideline_Note_March_2010FINAL.pdf"https://www.un.org/ruleoflaw/files/TJ_Guideline_Note_March_2010FINAL.pdf

*ለተጨማሪ መረጃ በቅርቡ የወጣውን What A Life! የሚለውን መፅሐፌን ማንበብ ይቻላል፡፡